# የኢትዮጵያ ሕዝባዊ አብዮታዊ ፓርቲ ( ኢሕአፓ)

Ethiopian People's Revolutionary Party (EPRP)

ሚያዚያ 25 ቀን 2000 ዓም
(May 3, 2008)

## ያለ ፕሬስ ነጻነት ዴሞክራሲ አይታሰብም!!

የዛሬ 15 ዓመት በዩኔስኮ አሳሳቢነትና አቅራቢነት የተ.መ.ድርጅት ጠቅላላ ስብሰባ ሜይ 3 ቀን 1993 አ.ም. እንደ አውሮፓ አቆጣጠር ዓለም አቀፍ የፕሬስ ነጻነት ቀን ሆኖ እንዲከበር ሲወስን በዓለም አቀፍ ደረጃ ለሕሊናቸውና ለዕውነት ተገዢ በመሆን በርካታ የጋዜጠኝነት ሙያ ያላቸው ተግባራቸውን ሲያከናውኑ ይደርስባቸው የነበረው ወከባ፥ ግድያ፥ እስራትና ለስደት መዳረግ በጣም የሚያስከፋ ነበር። ይህ ቀን አላማው ነጻና መድበላዊ ፕሬስ የተጠየቀበትን የዊንድሆክ መግለጫ ተብሎ በ1991 ዓ.ም. በናሚቢያ ከስምምነት የተደርሰበትን ውሳኔ ብቻ ሳይሆን በብዙ ሀገራት የኢንፎርሜሽንና የነፃነት መብቶች እየተጣሱ መሆናቸውንም የሚያስታውሰንም ጭምር ነው። በነፃ ፕሬስ አባላት ላይ የሚደርሰው በደል በአስከፊና በአምባገነን ሥርዓት ካሉ ሀገራት ባሻገር በሕገ መንግስታቸው ውስጥ የፕሬስና የሃሳብ ነፃነት ይከበራል በማለት ያወጁ መንግሥታት ሥር ለሚሰቃዩትና ለሚበደሉ ሁሉ የትግል አንድነት የሚገለጽበትም ነው። ባጠቃላይ ዕውነትን ፈልፍለው ለማውጣት በሚጥሩ ጋዜጠኞች ላይ በተለይ ሕጋዊነትን ባልተላበሰ ሁኔታ ሃይልን ተጠቃሚ በሆኑ ክፍሎች (እንደማፊያ ባሉ) ከፍተኛ ጫናና ዘመቻ የሚደረግባቸው ሲሆን፤ በሕዝብ ተቀባይነትን ባጡ አገዛዞች አማካኝነት ለእስርም ይዳረጋሉ። የሕዝብ መገናኛዎች ለአገዛዙ አመቺ እንዲሆኑ ለማድረግ ስራዎቻቸው ሳንሱር ይደረጋሉ ወይንም ደግሞ ይታገዳሉ። በጣም የሚያሳዝነውና ለማንም ለሀገሩ ቀናኢ ለሆነ ሁሉ በጣም አሳፋሪ የሆነው፤ በቅንነት ተግባራቸውን የሚያከናውኑ የነፃ ፕሬስ አባላት ለሞት የሚዳረጉ፣ ታስረው ደብዛቸው እንዲጠፋ የሚደረጉ ቁጥራቸው በየጊዜው እየጨመረ መሄዱ ነው።

በመሆኑም በዛሬው ቀን የፕሬስ ነፃነት በዓለም አቀፍ ደረጃ በሚከበርበት ወቅት በሀገራችን የፕሬስ ነፃነት ከምን ደረጃ ላይ እንዳለ መገምገምና መወያየት፤ መስዋዕት የሆኑትን ገድላቸውን በማስታወስ መዘከር ከሀገር ወዳድ ኢትዮጵያዊ ሁሉ የሚጠበቅ ነው። በኢትዮጵያ የመለስ አገዛዝ በአፋዊ ምንባብና በወረቀት ደረጃ የሕዝብን መብት እያከበርኩ ነኝ በማለት ስለ ፕሬስ ነፃነት፤ ስለ መድበላዊ ሥርዓት መስፈን መጠነ ሰፊ ፕሮፓጋንዳ ቢነዛም ሥልጣን ላይ ከተቆናጠጠ ጀምሮ ፕሬስን አስመልክቶ ያካሄዳቸው ተግባራት በሙሉ ጻረ ፕሬስ መሆኑን ያረጋገጡ በመሆናቸው የአምባገነን ጠባዩን ሊሸፍን አልተቻለውም። በዓለም አቀፍ ደረጃ የነፃ ፕሬስ ወዳጅ የሆኑ በርካታ ተቋማት የመለስ አገዛዝን በተለያዩ ጊዜያት መኮነናቸው የሚያመለክተው ይህንን እንጂ ሌላ አይደለም። የረጅም ጊዜ ተጋድሎ ውጤት ሆነው በማበብ ላይ የነበሩት የነፃ ፕሬሶች በመለስ አገዛዝ ታግደዋል። አባላቶቻቸው ታስረዋል፤ የተወሰኑቱ ለስደት ተዳርገዋል። በርካታዎች የሞት ጽዋ ተጎናጽፈዋል። አንዳንዶቹም ይህንን ሁሉ ተቋቁመው መጽሄትም ሆነ ጋዜጣ ለማሳተም እንዳይችሉና ለሕትመት እንዳይበቁ የማሳተሚያ ዋጋውን በከፍተኛ ደረጃ ስላስወደደባቸው ከገበያው ውጭ ለመሆን ተገደዋል።

በአሁኑ ወቅት ፕሬሱ - ጋዜጣው፥ ሬድዮና ቴሌቪዥኑ ባጠቃላይ የህዝብ መገናኛ ተቋማት ሁሉ በመለስ አገዛዝ ቁጥጥር ስር ናቸው። ነፃነታቸውን ጠብቀውና መብታቸውን አስከብረው ለመንቀሳቀስ የሚፈልጉትን ፈቃድ ከልክሏቸዋል። የፕሬስ ሕጎችን አስመልክቶ በተለያዩ በወንጀለኛ መቅጫ - በብሮድካስቲንግ፥ በንግድ፥ በማስታወቂያ ሚኒስቴር፥...ወዘተ ሕግ ውስጥ ሰንቅሮና ከፋፍሎ በማውጣት፤ በከፍተኛ ደረጃና ተንኮል በተሞላበት መልክ የሚገደቡበትን ሁኔታ አመቻችቷል። በዚህም የተነሳ ዜና(ኢንፎርሜሽን) የማግኘት ሕግና የፕሬስ ነፃነት ተደበላልቀው ለመለየት እንዲያስቸግሩ ብቻ ሳይሆን ዛሬ በወረቀት ደረጃ አለኝ ይል የነበረው የፕሬስ ነፃነት ጨርሶ እንዳይኖርም መሰረቱን ዳግም ለመጣል እየተዘጋጀ ነው። የባዕዳን አማካሪዎችን ድጋፍ ያገኘ በመሆኑ ከሀገር ወዳድ ኢትዮጵያዊያን በርካታ ተቃውሞ መደረጉ እምብዛም አላሳሰበውም። ላለፉት 18 አመታት የድርጅት ተለጣፊዎችን በመጠፍጠፍ የመድበለ ፓርቲ ሥርዓት እንደሰፈነ አድርጎ ለማጭበርበር እንደጣረው ሁሉ ከአገዛዙ ማስታወቂያ ተቋም በተለየ የራሱን ደጋፊ ጋዜጠኞች እንደልባቸው እንዲንቀሳቀሱ አድርጎ የፕሬስ ነፃነት እንዳለ ለማስመሰል ቢጥርም ሕዝብን ሊያሞኝ ግን አልተቻለውም። በዚህም፣ ወያኔ ቀደም ሲል እንደታየው ሁሉ አሁንም ከሽፎበታል። የፕሬስ ነፃነትና ዜና የማግኘት መብት በመለስ አገዛዝ በተለያዩ ደረጃዎች የተገደበ በመሆኑ ሕዝብ ስለ ሀገሩም ሆነ ስለወደፊት እጣው የመወሰን መብቱና ነፃነቱ ተገፏል።

የአሳ ግማቱ ከጭንቅላቱ መሆኑ እየተረሳ አለበለዚያም ሆን ብሎ ወደጎን በመተው፤ በተደጋጋሚ በታሰሩ የድርጅት መሪዎች መፈታትን አስመልክቶ ለመታዘብ እንደተቻለው መለስ ዜናዊ የሚያወራውና የሚናገረው በመመሪያነት የሚያገለግል እንዳልሆነ ሁሉ፤ አገዛዙ ያለ መለስ ዜናዊ፤ መለስ ያለ አገዛዙና ደጋፊዎች ገለባ መሆናቸው ግልጽ ሆኖ ሳለ የአገዛዙ አፈቀላጤዎች ሁለቱን እየለያዩ መለስን በተናጠል በማመስገን ሌላውን በመንቀፍ ለመሸፈን የሚያደርጉት ጥረት የትም አላስኬዳቸውም። በዚህ ዓይነት አገዛዝ/ሥርዓትም የፕሬስ ነጻነት ሊገኝ እንደማይቻል መገንዘብ ያዳገታቸው ሳይሆኑ ለማደናገሪያ የሚገለገሉበት መሆኑ ከተነቃባቸውም ጊዜያቶች አልፈዋል። አይቻልም፤ አታጭበርብሩ እንላቸዋለን። የፕሬስ ነፃነትን በዋናነት እየተፈታተነ ይበልጡኑ እያጨጨ ያለው የመለስ አገዛዝ ባጠቃላይ እንጂ አንዱ ለእድገት እየሰራ ሌላው ለውድቀት የቆመ አይደሉም። መለስ፣ ገዢው ፓርቲና አገዛዙ ለባዕዳን መደለያ ካልሆነ የአንድ ሳንቲም ሁለት ገጽታዎች መሆናቸው ፀሐይ የሞቀው እውነታ መሆኑን መሸፈን አይቻልም። በባዕዳን አማካሪዎች ከዚህም ከዚያም በመውሰድ ሆኖም ግን ከሀገራችን ተጨባጭ ሁኔታ ጋር ተጣጥሞ የማይሄድ የፕሬስ አዋጅ በወረቀት ላይና በነጋሪት ጋዜጣ ማወጅ ለማጭበርበር ካልሆነ ዋጋ የለውም። ደጋግመን እንደገለጽነው ጣጣውና ችግሩ የኢትዮጵያ ህዝብ እንደ ዐይን ብሌኑ እንዲመለከተው፤ እንደ ሕይወት እስትንፋሱ እንዲተነፍሰው የፕሬስ ነፃነትን ራሱ አምጦ እንዲወልደው አለመደረጉና ለዚህም መብቱን መነፈጉ ነው። በዚህ ግብግብ ምክንያት ነው በርካታ ለሀገራቸውና ለሕዝባቸው ቀናኢ የሆኑ ጋዜጠኞች የታሰሩት፤ የተሰደዱትና የሕይወት ግብር የከፈሉት። የነፃነት መብታቸው፥ ለእውነት ለመቆም ያላቸው

EPRP
P.O.Box 73337
Washington DC, 20056
USA
Tel. 202-291-4217 Fax 202-291-7645

E-mail : ESPIC@aol.com

Website: www.EPRP.com

EPRP
BP 22
Bois colombes 92270
France

መብት፥ እስካልተከበረ ጊዜ ድረስም ጸረ መለስ የሆነው ትግላቸው እንደሚቀጥልና የህዝብም ድጋፍ እንደማይለያቸው፤ የትግላቸው ማሳረጊያውም በሕዝቡ የበላይነት ሲደመደም ብቻ መሆኑ ለመለስና ለአገዛዙ በትግል ግልጽ ሊደረግላቸው ይገባል።

ዛሬ የፕሬስ ነፃነት በአግባቡ ቢኖር ኖሮ ለምሳሌ ባልተገራ የነፃ ገበያ ሥርዓቱ አማካኝነት እየደረሰ ያለውን የተዛባ የሀብት ክፍፍል፤ የፍትህ መታጣትና ልዩነት መስፋት፤ ስለኑሮ ውድነትና የሸቀጦች ዋጋ መናር፤ መሰረታዊ በሆኑ ሀገራዊና ሕዝባዊ ጥያቄዎች ብሔራዊ መግባባት መታጣት፤ ወዘተ ላይ የነጻ ፕሬሱ ተቋማት የሚያሳዩት ነፀብራቅ ለሙያቸው ብቃትነት ማረጋገጫ በሆነ ነበር። አገዛዙ እንደፈለገው የኤኮኖሚውን አቅጣጫ ለባዕዳን ጥገኛ ለማድረግ ባልተቻለውም ነበር። የኤኮኖሚ እድገት ተገኘ ተብሎ የሚለፈፈውን ፕሮፓጋንዳና የባዕዳን ምስክር ምንነትና ገለባነትን በሚገባ ማጋለጥ በተቻለ ነበር። ለባዕዳን ጥቅም ሲባል በሶማሌ የውስጥ ጉዳይ ጣልቃ በመግባት እሳካሁን ድረስ በምስጢር የተያዘው ምን ያህል የሕዝብ ሀብት ወጪ እንደተደረገና ምንስ ያህል ወታደር ለሞት እንደበቃ ለህዝብ በተጋለጠ ነበር። በርግጥም ጣልቃ ገብነቱ ብሔራዊ ደህንነት ማስገኘት አለማስገኘቱ በተጨባጭ በሕዝብ ውይይት ግልጽ ሊሆን በቻለም ነበር። ለዚህ መሰል ብሔራዊ ክህደትና የወንጀል ተግባራት በተለይም ደግሞ ለሙስና በዋናነት ተጠያቂ የሆኑት ተጋልጠው ከሥልጣን ወንበራቸው አንዲት ደቂቃ እንኳ ሊቀመጡ ሕዝብ ባልፈቀደላቸው ነበር።

የፕሬስ ነፃነት ከወረቀት ምንጣፍ አልፎ በአግባቡ ቢኖር ኖሮ ለመልካም አስተዳደር፤ ለግልጽነት መገኘት፤ ለማህበራዊ መረጋጋት ሕዝብም በፕሬሱ አማካኝነት የራሱን ሚና በመጫወት መልካም አስተዋጽኦ ባበረከተ ነበር። ለዴሞክራሲ ሥርዓት መገንባትና መዳበር መሰረት የሚሆነው የመደራጀትና በፖለቲካው ሂደት የመሳተፍ ነፃነት ከፍተኛ ዕድገትን ባስገኘ ነበር። ዛሬ የፕሬስ ነፃነትን ስናከብርና ስናስታውስ እነዚህንና ከነዚህ ጋር የተያያዙ ገና ምላሽ ያላገኙ ብሄራዊ ጉዳዮችን ከግንዛቤ በማስገባት ሲሆን ዛሬም እንደ ቀድሞው ለፕሬስ ነፃነት ገና ወሳኝ ትግል ማድረግ እንደሚገባ በማመልከት ነው። ለነፃነቱ ያልተጋለ፤ መብቱን በትግሉ የማያስከብር ህዝብ ሁሌም በሀገሩ ጥያቄ ወሳኝ ሊሆን አይቻለውም። በተወሰነ የታሪክ አጋጣሚ ሥልጣን የተቆናጠጡ ቀርቶ በሕዝብም ምርጫ ይሁንታን ያገኙ ቡድኖች የሕዝብን መብት ለመግፈፍ ዳዴ በሚሉበት ጊዜ ነቅቶ የማይከታተል ዜጋ ሁሌም ከበደል ነጻ ሊሆን አይቻለውም።

ሃሳብን በነጻ የመግለጽ መብት እንዲከበር ነጻ የፕሬስ አዋጅ በትግላቸው እንዲገኝ የታገሉና መስዋዕትነት የከፈሉትን ስንዘክር የወደፊቱን አርቆ በማየት ስለሆነ ኢሕአፓ ዛሬም እንደ ቀድሞው የነፃ ፕሬስ አባላት የሚያደርጉትን ትግል እየደገፈ ከጎናቸው እንደሚቆም ያረጋግጣል። ያለ ፕሬስ ነፃነት ዴሞክራሲ አይታሰብም።

የፕሬስ ነፃነት ይከበር ባሉ ለእስር የተዳረጉት ሁሉ ይፈቱ!

EPRP
P.O.Box 73337
Washington DC, 20056
USA
Tel. 202-291-4217 Fax 202-291-7645

E-mail : ESPIC@aol.com

Website: www.EPRP.com

EPRP
BP 22
Bois colombes 92270
France

የፕሬስ ነጻነት ያለገደብ ለሚሰፍንባት ኢትዮጵያ እንታገል!

EPRP
P.O.Box 73337
Washington DC, 20056
USA
Tel . 202-291-4217 Fax 202-291-7645

E-mail : ESPIC@aol.com
Website: www.EPRP.com

EPRP
BP 22
Bois colombes 92270
France